አዋጅ ቁጥር-----------/2014

## ስለ ዕጽዋት ዘር ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ የዕፅዋት ዘር ዘርፍ የግብርና ምጣኔ ሃብት ዕድገትን፣ የምግብ፣ ስነምግብ እና የመኖ እንዲሁም የደን ውጤቶችን ዋስትና ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዘላቂ የዕፅዋት ዘር ሥርዓት በመዘርጋት የዝርያ እና ዘር በብዛትና በጥራት ለአምራቾች እንዲቀርብ በማድረግ ሥርዓተ ምህዳር ላይ የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳደግ በማስፈለጉ፤

የግልና የመንግስትን የዕፅዋት ዘር ኩባንያዎች በማሳተፍ እና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ሥርፀት፣ ለምርትና ምርታማነት ዕድገትና ለምርት ጥራት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በላቀ ደረጃ ማሳደግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ አዋጅ "የዕፅዋት ዘር አዋጅ" ቁጥር ----------/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1/ "ዕፅዋት" ማለት ከእንስሳትና ከደቂቀ ዘአካላት ውጭ ያለ ማንኛውም ሕይወት ያለው የሚራባ አካል ነው፤

   2/ "ዘር" ማለት ለዕፅዋት ማራባት የሚያገለግል እውን ዘር፣ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ሥራ ሥር፣ ችግኝ፣ ሳየን፣መሰረተ ግንድ ወይም ሌላ ዓይነት የተክል አካል ነው፤

   3/ "ዝርያ" ማለት፡-

   ሀ) ከአንድ የተወሰነ ጄኖታይፕ ወይም ከብዙ ጄኖታይፖች ጥምረት በሚመነጩ ባህርያት መታየት ራሱን የሚገልጽ፤

   ለ) ካሉት ባህርያት ቢያንስ በአንዱ ከማናቸውም ሌሎች የዕፅዋት ምድብ የሚለይ፤ እና

   ሐ) ባህርያቱን ሳይቀይር መራባት በመቻሉ ምክንያት እንደ አንድ ምድብ ሊወሰድ የሚችል ነው፤

   4/ "ጄኖታይፕ" ማለት የአንድ ዕፅዋት የዘረ-መል ውቅር ነው፤

   5/ "ዝርያ መልቀቅ" ማለት የምርምር ሂደት ጨርሶ  የብቃት ማረጋገጫ እና የባሕርይ ልየታ ፍተሻ መስፈርት ሲያሟላ ዝርያው እንዲባዛ፣ እንዲመረት ፣ ዘሩ ለአገር ውስጥ ወይም ለውጭ አገር ገበያ እንዲሁም ለሌላ ተግባር ጥቅም ላይ እንዲውል በ ባለስልጣኑለመፍቀድ የሚያስችል ሂደት ነው፤

   6/ "ብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ" ማለት አንድ እጩ ዝርያን ለመጠቀም  ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ፋይዳውን በቅርብ ጊዜ ከተለቀቀ እና ከአካባቢ ዝርያ ጋር ለማወዳደር የሚደረግ ሙከራ ነው፤

7/ "የባሕርይ ልየታ ፍተሻ" ማለት ለተለያዩ የዕፅዋት አይነቴዎች የወጣውን ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ መስፈርት ዕጩ ዝርያው ማሟላት አለማሟላቱ የሚረጋገጥበት የሙከራ አይነት ነው፤

8/ "ነባር ዝርያ" ማለት በአርሶ/አርብቶ አደሩ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት የኖረና ከዚህ በፊት ያልተለቀቀ ዝርያ ነው፤

9/ "የዘር ደረጃ" ማለት አራቢን፣ቅድመ መስራችን፣ መስራችንና እስከ 3ኛው ትውልድ ያለውን የተመሰከረለት ዘርን የሚካትትነው፤

10/ "አራቢ ዘር" ማለት የመጀመሪያ የዘር ደረጃ ነው፤

11/ "ቅድመ መስራች ዘር" ማለት ከአራቢ ዘር የሚገኝ የዘር ደረጃ ነው፤

12/ "መስራች ዘር" ማለት ከቅድመ መስራች ዘር የሚገኝ የዘር ደረጃ ነው፤

13/ "የተመሰከረለት ዘር" ማለት በትውልዱ ከመስራች ዘር ወይም ከ1ኛው፣ ከ2ኛው ወይም ከ3ኛው ከተመሰከረለት ዘር የሚገኝ የዘር ደረጃ ነው፤

14/ "የጸደቀ ዘር" ማለት በአገር ውስጥ የተመረተ ወይም ከውጭ የገባ ሆኖ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ማሟላቱ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተረጋገጠ ዘር ነው፤

15/ "የአስቸኳይ ጊዜ ዘር" ማለት የተገኘበት ወይም ምንጩ የታወቀና አጣዳፊ የዘር እጥረት ሲያጋጥም ችግሩን ለመፍታት የሚውል ነው፤

16/ "የመጠባበቂያ ዘር" ማለት የዕፅዋት ዘር እጥረት እንዳያጋጥም አስቀድሞ የሚከማች ዘር ነው፤

17/ "ጥራቱ የተገለፀ ዘር" ማለት ዘጠና በመቶ በአምራቹና አስር በመቶ በክልል ባለስልጣን የጋራ ኃላፊነት የዘር ጥራት ማረጋገጥ ሥራ ተደረጎበት የሚቀርብ ዘር ነው፤

18/ "ገደብ የተጣለበት ዘር" ማለት በአገር ውስጥ ገበያ ላይ እንዳይውል፣ ወደ አገር እንዳይገባና ከአገርም እንዳይወጣ የተከለከለ ዘር ነው፤

19/ "ልውጥ ህያው" ማለት ሰው ሰራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ህያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ስለተከተተበት የዘረመሎቹ ይዘት ወይም የባህሪው ክስተት የተለወጠበት ሕያው ነው፤

20/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ሰው ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ማከፋፈል፣ መቸርቸር ላይ ለመሰማራት ሲፈልግ መስፈርት ማሟላቱ ሲረጋገጥ የሚሰጥ ነው፤

21/ "የዘር ጥራት ደረጃ" ማለት በአንድ የዘር ትውልድ የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመስክ እና የላቦራቶሪ ጥራት መስፈርት ነው፤

22/ "የዘር ጥራት ማረጋገጥ" ማለት አንድ ዘር የዘር ጥራት ደረጃ ማሟላቱ የሚፈተሸበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት ሂደት ነው፤

23/ "የቅድመ ቁጥጥር" ማለት የመነሻ ዘር ለቀጣይ የዘር ብዜት ተግባር ከመዋሉ በፊት የሚካሄድ የዝርያ ጥራት ማረጋገጥ ሂደት ነው፤

24/ "ድህረ ቁጥጥር" ማለት ለቀጣይ ዘር ብዜት የማይውል የተመሰከረለትን ዘር የዝርያ ጥራት የሚረጋገጥበት ሂደት ነው፤

25/ "የዘር ኢንስፔክተር" ማለት በመስክና በላቦራቶሪ የዘር ጥራትን እንዲያረጋግጥ በባለስልጣኑ የሚሰየም ሰው ነው፤

26/ "አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር" ማለት በሕግ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርትፍኬት የተሰጠው፣ የመሬት ይዞታው ከ10 ሄክታር ያልበለጠና በዋናነት የራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት

በመጠቀም የግብርና ልማት የሚያካሂድና ኑሮው በዋናነት በግብርና ላይ የተመሰረተ አርሶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ነው፤

27/ “የአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ዝርያ” ማለት፤

ሀ) በአርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች መሬት ላይ በባህላዊ መንገድ የለማ እና የበለፀገ፣ ወይም

ለ) አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች በዋነኛነት ከተለያዩ የዕፅዋት ምንጮች ያዳቀሉት ወይም የመረጡት፣ዝርያ ነው፤

28/ “ራስ አገዝ የዘር ጥራት ማረጋገጥ” ማለት በባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኘ አምራች ያመረተውንና ያዘጋጀውን ዘር ራሱ በዘር ጥራት ደረጃ መሰረት አረጋግጦ የሚሸጥበት ሂደት ነው፤

29/ “የሶስተኛ ወገን የዘር ጥራት ማረጋገጥ” ማለት አምራች ያልሆነ ግን በባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኘ ሰው የዘርን ጥራት የሚያረጋግጥበት ሂደት ነው፤

30/ “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን ነው፤

31/ “የክልል ባለስልጣን” ማለት በክልል የዘር ጥራትን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው አካል ነው፤

32/ “ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

33/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ነው፤ ፤

34/ “ቢሮ” ማለት የክልል ግብርና ቢሮ ነው፤

35/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት ሙብት የተሰጠው አካል ነው፤

36/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1/ ይህ አዋጅ በማንኛውም ዘር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ፡

ሀ) ማንኛውም ሰው ካመረተው ምርት ላይ ጠብቆ በሚጠቀምበት ዘር፤

ለ) አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ወይም አርብቶ አደሮች መካከል ከምርቱ ጠብቆ እርስ በርስ በሚደረግ ልውውጥ ወይም ሽያጭ፤

ሐ) ለምርምር እና ትምህርት ሥራ በሚውል ዘር

ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ዝርያ መልቀቅና መመዝገብ</u>

4. <u>ዝርያዎችን ስለመልቀቅ</u>

1/ ባለስልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ:-

ሀ) ዕጩ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ እና የባህርይ ልየታ ሙከራ በራሱ በመስራት በዝርያ ገምጋሚ ኮሚቴዎች በማስገምገም እና ብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ፤ ወይም

ለ) የብቃት ወይም የባህርይ ልየታ ወይም ሁለቱንም ሙከራ በእጩ ዝርያ  አመልካች እንዲሰራ በማድረግ በብሔራዊ ዝርያ ገምጋሚ ኮሚቴዎች በማስገምገም እና በዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ አንዲሰጥ በማድረግ፤ ወይም

ሐ) በውጭ አገር ዕውቅና ባለው ተቆጣጣሪ አካል የተሰራ የዝርያ የባህሪ ልየታ እና በአመልካቹ የአገር ውስጥ የማላመድ ሪፖርት በመቀበል፤

የዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ የአሰራር ሥርዓትን ተግባራዊ ያደርጋል፤ዝርዝር አፈጻጸሙም በመመሪያ ይወሰናል፤

2/ ባለስልጣኑ በየትኛው የዝርያ ለቃቃና ምዝገባ የአሰራር ሥርዓት ማለፍ ስላለባቸው  የዕፅዋት ዓይነቴዎች ዝርዝር አግባብነት ባለው መገናኛ ብዙኃን እንዲገለጽ ያደርጋል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከባለስልጣን ጋር በመመካከር፤

ሀ) በዓይነታቸው ልዩ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው እና የተለዩ በውጭ አገር የተመዘገቡ ዝርያዎች በአገር ውስጥ የዝርያ ማላመድ  ሙከራ ማካሄድ ሳያስፈልግ በቀጥታ እንዲመረቱ ሊፈቅድ ይችላል

ለ) ከላይ ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ዝርያው ልዩ ሃገራዊ ፋይዳ በጽሁፍ መቅረብ ይኖረበታል፤

4/ ሆኖም በንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተጠቀሰው ልዩ ሁኔታ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ባለስልጣኑ ዝርያው:

ሀ) ከሌሎች ዝርያዎች የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህርይ ሪፖርት መቅረቡን፤

ለ) የአገሪቱ የብዝሃ ሕይወት እና የኳራንቲን መስፈርት መሟላቱን፤

በማረጋገጥ ጥቅም ላይ አንዲውል ይደርጋል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "1/ሐ/"፣ "3" እና "4" መሰረት አንድ የዕፅዋት ዝርያ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ መመረት ከጀመረ በኋላ በዝርያው ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት የዝርያው ባለቤት ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል፤

6/ ዘሩን ወይም ምርቱን አባዝቶ ለውጭ አገር ገበያ ለመላክ ዓላማ የሚውል ማንኛውም ያልተመዘገበ ዝርያ ወደ አገር በሚገባበት ወቅት አግባብነት ያላቸው የጀነቲክ ሃብት አጠቃቀም እና የኳራንቲን ሕጎችን ማሟላቱ ተረጋግጦ የዝርያ የማላመድ ሙከራ ማካሄድ እና በዝርያ መዝገብ መመዝገብ ሳያስፈልግ፣ በአገር ውስጥ ተባዝቶ ቀጥታ ወደ ውጭ ይላካል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይገለጻል፤

7/ ባለስልጣኑ:-

ሀ) የዕጩ ዝርያዎችን ብቃት የሚገመግሙ ቴክኒካል ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

ለ) ከመመረት ውጭ የሚሆኑ የእጽዋት ዝርያዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ኮሚቴ ያቋቁማል፤

ሐ) የቴክኒካል ኮሚቴዎችን ሪፖርቶች መሠረት በማድረግ ዕጩ ዝርያዎች ላይ እና ከመመረት ውጭ በሆኑ ዝርያዎች ላይ ውሳኔ የሚሰጥ ብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

መ) የሚቋቋሙት ኮሚቴዎችን ስብጥር እና አሰራር በዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ ይወሰናል።

ሠ) የዝርያ ብቃት አረጋጋጭ ባለሙያ ይመድባል፤

5. <u>ብሔራዊ የዝርያ መዝገብ</u>

ባለስልጣኑ:-

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት ዝርያዎችን በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል፤

2/ አገሪቱ አባል በሆነችባቸውና ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የዝርያ መዝገብ ላይ የተመዘገቡትን ዝርያዎች ተቀብሎ በዝርያ መዝገቡ ያካትታቸዋል፤

3/ በተለያየ ምክንያት ከመመረት የወጡ ዝርያዎች ከዝርያ መዝገብ ይሰርዛል።

## ክፍል ሦስት

## የእጽዋት ዘር ማምረት፣ ዝግጅትና ግብይት

6. ስለ ዘር ማምረት ዕቅድ

1/ ማንኛውም ለገበያ የሚሆን ዘር በማምረት የሚሰማራ ሰው ስለሚያመርተዉ ዘር ዕቅድ ለባለስልጣኑ ወይም ለክልል ባለስልጣን አስቀድሞ በሚወሰን ጊዜ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

2/ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን አገራዊ መረጃዎች የያዘ የዘር ምርት መረጃ ቋት ያዘጋጃል፤

ሀ) ዓመታዊ የምርት ዕቅድና የፈጻሚዎች የኃላፊነት ድርሻ፤

ለ) ዓመታዊ የዘር ምርት በዝርያ ዓይነት፣ በዘር ደረጃ፣ በአምራችና በጥቅል፤

ሐ) ዘር ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለ መሬት፣ መሠረተ ልማት እና ሌሎች ግብዓቶች፤ እና

መ) ለብሔራዊ የዘር ምርት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መረጃዎች፤

3/ የዘር ምርት መረጃ ቋት ከዘር አምራቾችና አከፋፋዮች መዝገብ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት::

7. የዕጽዋት ዘር ማምረት

1/ ማንኛውም ሰው

ሀ) በዓመታዊ ሰብሎች ዘር ማምረት ለመሰማራት፤

ለ) በደንና በፍራፍሬ እንዲሁም ሌሎች ቋሚ ሰብሎች የዘር ምንጭነት አገልግሎት ለመስጠት የእናት ዛፍ እና የማምረቻ ቦታውን ማስመዘገብ፤

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

ሐ) ለገበያ የሚሆን የተመሰከረለት ዘር ወይም መስራች ዘር ወይም ሁለቱንም በማምረት ተግባር ላይ ከመሰማራቱ በፊት ለእነዚህ የዘር ደረጃዎች ተብሎ የተዘጋጀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

መ) አራቢ ዘር እና ቅድመ መስራች ዘር ለማባዛት የሚፈልግ ከሆነ እነዚህን የዘር ደረጃዎች ለማባዛት የሚያስችለውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከባለስልጣኑ ወይም ከክልል ባለስልጣን ማግኘት አለበት፤

ሠ) በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑትን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 "ሐ" እና "መ" የተጠቀሱትን ሁለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ከማግኘት አይከለከልም፤

ረ) ሌሎች ዝርዝር አፈጻጸሞች በመመሪያ ይወሰናል።

2/ ለገበያ የሚሆን ዘር በማምረት ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፤

3/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ዘር አምራች አግባብነት ባለው ማንኛውም ሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገቡ ዝርያዎችን አራቢ ዘር፣ ቅድመ መሥራች ዘር እና መሥራች ዘርን ከሚያባዙ ተቋማት ማግኘት ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

4/ በዘር ማምረት የተሰማራ ሰው የሚያመርተውን ዘር ምንጭ፣ ዘር ደረጃና ሌሎች የጥራት መስፈርቶችን ለባለስልጣን ወይም ለክልል ባለስልጣን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

5/ ማንኛውም ዘር አምራች ሆኖ ዘር በማምረት ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው በራሱ መሬት ወይም በሌሎች አምራቾች መሬት በውል ላይ ተመስርቶ ዘር ማምረት ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

8. <u>የዘር ዝግጅት</u>

ማንኛውም ሰው በዘር ዝግጅት ለመሰማራት ሲፈልግ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል.

9. <u>የዘር ግብይት</u>

1/ በዚህ አዋጅ የዘር ግብይት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ወደ ውጭ መላክ፤

ለ) በአገር ውስጥ ማከፋፈል እና መቸርቸር፤

ሐ) የደንና የፍራፍሬ ዘር መልቀም፤

መ) ማከም፣ ማሰራጨት፣ ማጓጓዝ፣ማከማቸት፤ እና

ሠ) ሌሎች የግብይት ዓይነቶችን አስመልክቶ በመመሪያ ይወጣል፤

2/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) በአገሪቱ ከአንድ ክልል በላይ በዘር ግብይት ተግባር ላይ የሚሰማራ ከሆነ ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

ለ) በአንድ ክልል በመወሰን በዕፅዋት ዘር ግብይት ተግባር ላይ የሚሰማራ ከሆነ ከክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

ሐ) የመንግስት ዝርያዎች መነሻ ዘር በመጠቀም ዘር የሚያመርትና ለገበያ የሚያቀርብ ከሆነ ያልተዋወቁ አዳዲስ የመንግስት ዝርያዎችን የማስተዋወቅ ግዴታ ይኖርበታል፤

3/ የዕጽዋት ዘር ግብይት በግል፣ በማህበራት፣በመንግስት ወይም በሌሎች አቅራቢዎች ሊከናወን ይችላል፤

4/ የዘር ግብይት ስርዓቱ ዝርዝር አፈጻጸም አስመልክቶ በመመሪያ ይወጣል፤

10. <u>የዘር ግብይት የስራ ወሰንን ስለማስፋት</u>

በአንድ ክልል ተወስኖ ይሰራ የነበረ የዘር አምራች ወይም አዘጋጅ ወይም አከፋፋይ ከአንድ ክልል በላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ከሆነ አስቀድሞ በክልል ውስጥ ይሰራበት የነበረውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለክልል ባለስልጣን መመለስ እና መስፈርቶችን በማሟላት ከባለስልጣኑ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል።

11. <u>የመጠባበቂያ ዘር ሥርዓት</u>

ሚኒስቴሩ የዘር እጥረት እንዳይከሰት አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የመጠባበቂያ ዘር ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙም በሚኒትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል::

12. <u>የመረጃ አያያዝ</u>

ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን ዘርን በተመለከተ መረጃን ይመዘግባል፤ ያደራጃል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ተደራሽ ያደርጋል::

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የዘር ጥራት ኢንስፔክሽንና ማረጋገጥ</u>

13. <u>የዘር ጥራት ደረጃ</u>

ባለስልጣኑ የዘር ጥራት ደረጃ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስትቲዩት ጋር በትብብር ያወጣል፤ መተገበሩንም ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥራ ያከናወናል።

14. <u>የዘር ጥራት ፍተሻ ላብራቶሪዎች</u>

1/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) በአገር ውስጥ የሚገኙ የዘር ላብራቶሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የዘር ጥራት ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት እንዲጠቀሙ ያመቻቻል፤

ለ) የዘር ላብራቶሪዎች አግባብ ባለው አገር አቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ አካል እውቅና እንዲያገኙ መስፈርቶች ያስተዋውቃል፤ ይደግፋል፤

ሐ)በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው አገራዊ የዘር ላብራቶሪ ያቋቁማል ወይም ይሰይማል፤

መ) በክልል የሚገኙ የመንግስት ወይም የግል ወይም የማህበራት ዘር ላብራቶሪዎች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በየጊዜው ያረጋግጣል፤

ሠ)የክልል ባላስልጣን ዘር ላቦራቶሪዎች የፍተሻ ብቃት ለመገምገም ናሙና ይወስዳል፤አገራዊ የፍተሻ አሰራር መጣጣም እንዲኖርም በትብብር ይሰራል፤

2/ የዘር ላቦራቶሪዎች በናሙና አውጭ ወይም በኢንስፔክተር በሚቀርብላቸው ናሙና መሰረት የጥራት እና ጤንነት ፍተሻ ያከናውናሉ፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

15. <u>የዘር ጥራት ኢንስፔክሽን</u>

1/ የዘር ጥራት ኢንስፔክሽን ተግባር

ሀ) በአገር ውስጥ ተመርቶ ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ዘር በሚመረትበት ወይም በሚዘጋጅበት ቦታ በ ባለስልጣኑይከናወናል፤

ለ) በአገር ውስጥ ተመርቶ ለአገር ውስጥ ገበያ ለሚቀርብ ዘር በሚመረትበት ወይም በሚዘጋጅበት ወይም በሚሸጥበት ቦታ በክልል ባለስልጣን ይከናወናል፤

2/ ባለስልጣኑ እና እያንዳንዱ የክልል ባለስልጣን የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ የግል ወይም የመንግስት የዘርያ ብቃት አረጋጋጭ ባለሙያዎች፣ የዘር ኢንስፔክተሮችን ወይም የላቦራቶሪ አናሊስቶችን ይሰይማሉ።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተመደበ የዘር ኢንስፔክተር፡-

ሀ) ከዘር ጥራት ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን በምርመራ ለማረጋገጥ የዘር ናሙና ይወስዳል፤ለዘር ላቦራቶሪ ያስረክባል፤

ለ) በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸም አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች፣ የማስገቢያ ፈቃዶች፣ መዛግብቶችና ሌሎች ሰነዶች እንዲቀርቡለት መጠየቅና መመርመር እንዲሁም ኮፒ ማድረግ ይችላል፤

ሐ) በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በማናቸውም የመንግስት የስራ ሰዓት ወደ ማናቸውም ዘር ማምረቻ ቦታ፣ ዘር መጋዘን ወይም ዘር ማዘጋጃ ተቋም በመግባት ወይም በማናቸውም ሰዓት ማንኛውንም ዘር የጫነ ተሽከርካሪ በማስቆም ኢንስፔክሽን ማካሄድ ይችላል፤

መ) ኢንስፔክሽን ሲያካሄድ ከባለስልጣኑን ወይም ከክልል ባለሥልጣን የተሰጠውን የመታወቂያ ካርድ ለሚመለከተው ሰው ማሳየት አለበት፤

ሰ) የዘር ኢንስፔክተር የዘር ኢንስፔክሽን ሲያከናውን ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፤

4/ የላቦራቶሪ አናሊስት ይህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ስለ ላቦራቶሪ የደነገጉትን ተግባራት ተፈጻሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚቀርብበት ናሙና መሰረት የጥራት ፍተሻዎችን ያካሂዳል፤ውጤቱን ይገልጻል፤

5/ ባለስልጣኑ በአገር አቀፍ ደራጀ ተመሳሳይነት ያለው የኢንስፔክሽን አሠራር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለክልሎች የጥራት ቁጥጥር ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣል።

16. <u>የዘር ጥራት ማረጋገጥ</u>

1/ በአራቢ ዘር፣ በቅድመ መስራች ዘር፣ በመስራች ዘር፣ በተመሰከረለት አንደኛ፣ሁለተኛ እና ሦስተኛ ትውልድ ዘር፣ ጥራቱ በተገለጸ እንዲሁም በአስቸኳይ ጊዜ ዘር ተግባራዊ ይሆናል፤

2/ በሚከተሉት አማራጭ የዘር ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት አቅራቢዎች ሊከናወን ይችላል፡

ሀ)ሙሉ በሙሉ በባለስልጣኑ ወይም በክልል ባለስልጣን፤

ለ) ጥራቱ በተገለጸ ዘር ጥራት ማረጋገጥ ሥርዓት፤

ሐ) በራስ አገዝ የዘር ጥራት ማረጋገጥ፤ ወይም

መ)በሶስተኛ ወገን የዘር ጥራት ማረጋገጥ፤

3/ የክልል ባለስልጣን:-

ሀ) ለራስ አገዝ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ለመሰማራት ለሚፈልግ ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ለ) በክልሉ ለሚመረት፣ ለሚዘጋጅ፣ለሚከማች እና ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብን ዘር ጥራት ያረጋግጣል፤

4/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጹትን የጥራት ማረጋገጥ አማራጭ አሰራሮች እና ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይገለጻል፤

ለ) ከውጭ የሚገባ ዘር ከኢትዮጵያ ዘር ጥራት ደረጃዎች ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፤

ሐ) በአገር ውስጥ ተመርቶ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ዘር ከተቀባዩ አገር ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከዓለምአቀፍ ጥራት ደረጃ ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፤

መ) ከሃገር ውጭ ለተቋቋሙ ለማናቸውም ከኢትዮጵያ ዘር ጥራት ምርመራና ማረጋገጥ ስርዓት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ብሎ ላመነባቸው የዘር ጥራት አረጋጋጭ ድርጅቶችና ለምርመራ ውጤታቸው እውቅና ሊሰጥ ይችላል፤

ሠ/ ሲጠየቅ በአንድ ክልል መመረቱ ተረጋግጦ በሌላ ክልል ለሚከማች ዘር የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ይሰጣል፤የዘር ጥራት ደረጃ ላሟላ ዘር የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ምልክት ይሰጣል::

17. <u>የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

1/ የክልል ባለሥልጣን በክልሉ ውስጥ ተመርቶና ተዘጋጅቶ ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ ዘር፡-

ሀ) ዝርያው በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው የተመረተና የተዘጋጀ መሆኑን፤

ሐ) በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው መሰረት ጥራቱ የተፈተሸና ከዘር ጥራት ደረጃ መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤ እና

መ) አዋጁን ተከትሎ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን፤

ሲያረጋግጥ የዘር ጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለጸደቀ ዘር ይሰጣል።

2/ ባለስልጣኑ ከውጭ የገባ ዘር፡-

ሀ)በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ከተመዘገበ ዝርያ የተገኘ መሆኑን፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው የዘር አስመጪ የገባ መሆኑን፤

ሐ)በዚህ አዋጅ መሰረት የተመረመረና ከዘር ጥራት ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤ እና

መ) አዋጁን ተከትሎ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን፤ሲያረጋግጥ የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3/ ባለስልጣኑ ወደ ውጭ የሚላክ ዘር፡-

ሀ) በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ የተመዘገበ ዝርያ መሆኑን፤

ለ) የተመረተውና የተዘጋጀው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው መሆኑን፤ እና

ሐ) አዋጁን ተከትሎ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን፤ሲያረጋግጥ የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

4/ ማንኛውም የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡-

ሀ) በሀሰተኛ፣ በተሳሳተ ወይም ባልተሟላ መረጃ የተገኘ ከሆነ፤ ወይም

ለ) የቅድመ ወይም ድህረ ቁጥጥር ሙከራ ወይም የድጋሚ የዘር ላቦራቶሪ ፍተሻ ተካሂዶ የዘር ጥራት ደረጃዎች አሟልቶ ካልተገኘ፤

ይሰረዛል፤

5/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ከመሰረዙ በፊት ለባለቤቱ በማሳወቅ ቅሬታው የሚደመጥበትን እድል ይሰጠዋል።

18. <u>የዘር ጥራት ማረጋገጫ መለያ ምልክት ስለማድረግ</u>

ማንኛውም ዘር ባለስልጣኑን ወይም የክልል ባለስልጣንን የዘር ጥራት ማረጋገጫ መለያ ምልክት ሳይደረግበት ለአገር ውስጥ ወይም ለውጭ ገበያ ሊቀርብ አይችልም።

19. <u>ቅድመ ወይም ድህረ ቁጥጥር</u>

የክልል ባለስልጣን ማንኛውም የጸደቀ ዘር፦

ሀ/ የቀጣይ ዘር ደረጃ ለማምረት ተግባር ከመዋሉ በፊት በጥራቱ ላይ በቂ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቅድመ-ጥራት ፍተሻ ያካሂዳል፤ የተገኘው ውጤት ከዘር ጥራት ደረጃ ጋር ካልተጣጣመ የጸደቀው ዘር ለቀጣይ ዘር ደረጃ ብዜት እንዳይውል ያደርጋል፤

ለ/ የጥራት ደረጃ መስፈርት ሳያሟላ የጥራት ማረጋገጫ መስጠቱን ወይም መቀየጡን ለመጠርጠር ምክንያት ሲኖር ከተሰራጨው ዘር ላይ ናሙና ወስዶ ድህረ ቁጥጥር ፍተሻ ያካሂዳል፤የተገኘው ውጤት ከዘር ጥራት ደረጃ ጋር ካልተጣጣመ ሥርጭት እንዲቋረጥ ያደርጋል፤ ተጎጂዎች የሚካሱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

20. <u>የዘር ጥራት ደረጃ ስለማያሟላ ዘር</u>

1/ ፍተሻ የተደረገበት ዘር የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ካላሟላ የዘር ጥራት ደረጃው ዝቅ እንዲል ወይም ውድቅ እንዲሆን ይደረጋል፤

2/ የዕጽዋት ዘር ውድቅ እንዲሆን የተደረገበት ማንኛውም ሰው የሚከተሉት አማራጮች ሊሰጡት ይችላሉ፡-

ሀ) በሰው፣ በእንስሳት፣ በአካባቢ እና በአጎራባች ዕጽዋት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሌለው በራሱ መሬት ላይ መዝራት ፤ ወይም

ለ) የዕጽዋት ዘሩ የተበከለ፣ በኬሚካል የታሸ ወይም በማናቸውም ምክንያት ለምግብ ወይም ለመኖ አገልግሎት የማይውል ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ለምግብነት ወይም ለመኖነት እንዲውል ለገበያ ማቅረብ፤

3/ ውድቅ እንዲሆን የተደረገ ዘር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ሆኖ ሲገኝ በመመሪያ መሠረት እንዲወገድ ይደረጋል።

21. <u>የዕጽዋት ዘር ከውጭ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለመላክ</u>

ማንኛውም ሰው

1/ ዘር ከውጭ አገር አስገብቶ የሚያከፋፍል ወይም ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ ከ ባለስልጣኑየብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

2/ የማስገቢያ ወይም የመላኪያ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ካልተሰጠው በስተቀር ዘርን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ወደ ውጭ መላክ አይችልም፤

3/ ለዘር ማባዛት ዓላማ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ የማንኛውም ዝርያ ዘር አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ሥር በተገለጸው መሰረት ማስገባት አለበት፤

4/ ዘር ከውጭ አገር አስገብቶ ከዘር ማምረት እና ግብይት ውጭ ለሆነ አገልግሎት የሚያውለው ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይጠበቅበትም፤

5/ ልውጥ ህያው ያለው ዘር ወደ አገር ውስጥ ሊያስገባ የሚችለው የባለስልጣኑ አግባብ ካለው ህግ ጋር ስለመጣጣሙ ሲያረጋግጥ ይሆናል፤

6/ ገደብ የተጣለበትን ዘር ወደ ውጭ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አይችልም፤

7/ በሁለተኛው ትውልድ ራሱን የማይደግም ዘረ-መል ቴክኖሎጂ ያለበትን ዘር ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አይችልም።

22. <u>የአስቸኳይ ጊዜ ዘር ስለማቅረብ</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ አጣዳፊ የዘር እጥረት ሲያጋጥም ሚኒስቴሩ የአስቸኳይ ጊዜ

የዕጽዋት ዘር እጥረት መፈጠሩን በይፋ የማሳወቅና ችግሩ ላጋጠማቸው አካባቢዎች እንዲቀርብ የመፍቀድ ሥልጣን ይኖረዋል፤ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል::

## ክፍል አምስት

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

23. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ አመልካቹ በመመሪያ የተወሰኑትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተጠየቀውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን የአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ የክልከላውን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

3/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቀይበት ጊዜና የሚታደስበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

24. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድና መሰረዝ

1/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን ሁኔታዎች ጠብቆ ማቆየት ካልቻለ፤ ወይም

ለ) ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብን ወይም መመሪያን ተላልፎ ሲገኝ፤

ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን ጉድለቶቹን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስተካክል በማስገንዘብ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል።

2/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡

ሀ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ ወይም

ሐ) የዚህን አዋጅ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ ከተገኘ፤

ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ሊሠርዝ ይችላል፤

መ) ባለስልጣኑ ወይም የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እንደሰረዘ በምስክር ወረቀቱ ላይ ተመስርቶ የተሰጠው የንግድ ፈቃድ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጭ አካል በጽሁፍ ያሳውቃል።

25. መረጃ ስለመያዝና ተደራሽ ስለማድረግ

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘ ሰው፡-

1/ እንደአግባቡ የእያንዳንዱን ዘር የማምረቻ ቦታ፣ የተመረተ፣ የተዘጋጀ፣ ከውጭ ያስመጣውን፣ ወደ ውጭ የላከውን፣ ያከፋፈለውን ወይም የቸረቸረውን ዘር በዝርዝር መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፤

2/ እነዚህን መረጃዎች በባለስልጣኑ ወይም በክልል ባለስልጣን ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26. ስለ ትብብር

1/ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር እንዲቻል ባለስልጣኑ እና የክልል ባለስልጣናት እርስ በርሳቸው በትብብር ይሰራሉ፤

2/ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለመተግበር በሚያስችል መልኩ ሚኒስቴሩ እና ቢሮ የየራሳቸውን የዘር አማካሪና አስተባባሪ አካላትን ሊያደራጁ ይችላሉ። አፈጻጸሙም በመመሪያ ይወሰናል፤

3/ የፌደራል እና የክልል መንግስታት

ሀ) በዘር ዘርፉ ለተሰማሩ ወይም ለሚሰማሩ የዘር አምራች እና ግብይት ድርጅቶች ወይም ተቋማት የማበረታቻ ሥርዓት በትብብር ይዘረጋሉ፤

ለ) ብሔራዊ የዘርያ ብቃት ማረጋጋጫ ፣ የዝርያ ባህሪ ፍተሻ፣ የቅድመ እና ድህረ ቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ የሙከራ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ በጋራ ይሰራሉ::

27. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

የቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ በአስተዳደር ሥነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

28. ወንጀል እና ቅጣት

የዚህን አዋጅ ድንጋጌ እንዲሁም ይህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

29. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

30. የተሻሩ ህጎች

የዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

31. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ----------- ቀን --------------/2014 ዓ.ም

ፕሬዝዳንት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ